# የ COVID-19 ክትባቶች፡- ማወቅ ያለብን ነገር

| የት መከተብ እችላለሁ? | ቀጠሮ እንዴት ነው የምይዘው? |
|---|---|
| የጤና አቅራቢዎ | አቅራቢዎ ጋር ይደውሉ ወይም በመስመር ላይ ቀጠሮ ይያዙ |
| የጅምላ ክትባት ክሊኒኮች | ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ፡- vaccinelocator.doh.wa.gov/<br>ወይም በ 1-800-525-0127 ይደውሉ፣ በመቀጠል # ን ይጫኑ። የቋንቋ ድጋፍን ማግኘት ይቻላል። |
| አካባቢያዊ የመድኃኒት መደብሮች | |
| ወይም የማህበረሰብ ክሊኒኮች | ይለያያል። ስለ ክሊኒኩ ከጓደኛ ወይም የማህበረሰብ አባል ሊሰሙ ይችል ይሆናል። እንዴት መመዝገብ እንደሚችሉ ይጠይቋቸው። |

## ለ ክትባት ቀጠሮዬ ምን ይዤ መምጣት አለብኝ?

የሚከተሉትን ሊጠየቁ ይችላሉ፣ ግን ለእነርሱ መስጠት አያስፈልግዎትም፡-

- መታወቂያ
- የመድን ዋስትና ካርድ
- የማህበራዊ ደህንነት ቁጥር



ክትባቱን ለመውሰድ የአሜሪካ ዜጋ መሆን የለብዎትም። ስለ ስደተኛነት ሁኔታዎ አይጠይቁዎትም።

የግል መረጃዎች ለህዝብ ጤና አገልግሎት ብቻ ይውላሉ።

## ክትባቱ ምን ያህል ያስከፍላል?

ክትባቱን ያለ ምንም ወጪ ያገኛሉ። ምንም ዓይነት ክፍያ ወይም ሒሳብ እንዲከፍሉ መደረግ የለበትም።

## ሁለተኛ ክትባት ያስፈልገኛል?

አንዳንዶቹ ክትባቶች ባለ ሁለት መጠን ናቸው። ለበለጠ መከላከያ ሙሉ በሙሉ ከተከተቡ በኋላ ሁለት ሳምንታት ይወስዳል። አንዳንድ ሰዎች የማጠናከሪያ መጠን ሊፈልጉ ይችላሉ።

| | |
|---|---|
| Pfizer-BioNTech | 2 መጠኖች፣ በ 21 ቀናት ልዩነት |
| Moderna | 2 መጠኖች፣ በ 28 ቀናት ልዩነት |
| Johnson & Johnson | 1 መጠን |

**ለተጨማሪ መረጃ**

የሚከተሉትን ይጎብኙ፡- COVIDVaccineWA.org ወይም DOH.WA.GOV/Coronavirus

በዚህ ይደውሉ፡- 1-800-525-0127 ፣ በመቀጠል # ን ይጫኑ። የቋንቋ ድጋፍን ማግኘት ይቻላል።

Vaccinate WA

CovidVaccineWA.org

## የጎንዮሽ ጉዳቶቹ ምንድን ናቸው?

የጎንዮሽ ጉዳቶች ሊኖሩዎት ይችላል።

**በመላ ሰውነትዎ ላይ፡-**



- የድካም ስሜት
- የራስ ምታት
- የጡንቻ ሕመም
- ብርድ፣ ብርድ ማለት
- ትኩሳት
- ማቅለሽለሽ

**ክትባቱን በተከተቡበት ክንድዎ ላይ፡-**



- ሕመም ስሜት
- መቅላት
- ማበጥ

በሁለት ጊዜ ለሚሰጡ ክትባቶች፣ በሁለተኛ ጊዜ በሚሰጠው ክትባት ወቅት የጎንዮሽ ጉዳቶቹ ከበድ ሊሉ ይችሉ ይሆናል።

የአለርጂክ አጸፋዊ መልስ ካለዎት ወደ 911 ይደውሉ። ማናቸውንም ዓይነት የጎንዮሽ ጉዳት ሪፖርት ለማድረግ V-safe ላይ በዚህ አድራሻ ይመዝገቡ፡- vsafe.cdc.gov (በእንግሊዘኛ ብቻ የሚገኝ)።

## አንዱ ክትባት ከሌሎቹ ይሻላል?

ከ ባለ አንድ-መርፌው Johnson & Johnson (J&J) ክትባት ይልቅ የ mRNA COVID-19 ክትባት (Pfizer-BioNTech ወይም Moderna) እንመክራለን።

ነገር ግን J&J ሊያገኙ ከፈለጉ አሁንም ይገኛል። ስለ አማራጮችዎ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ያነጋግሩ።



## የ COVID-19 ክትባት ምን ያደርጋል?



የ COVID-19 ክትባት እንዳይታመሙ የሚከላከሉ የበሽታ መከላከያዎችን ለመገንባት ሰውነትዎን ያሰለጥናል።

## ክትባቶቹ የደህንነት ስጋት የሌለባቸው ናቸው?

አዎ። ሁሉም ክትባቶች **በአስር ሺዎች** በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ ተሞክረዋል።

ብዙ ዘሮች እና ከመጠን በላይ ውፍረት፣ የስኳር በሽታ፣ የልብ ህመም፣ የጉበት በሽታ እና ኤች.አይ.ቪ ባላቸው ሰዎች ላይ የደህንነት ስጋት እንደሌላቸው ታይተዋል።





የ Department of Health (ጤና መምሪያ) የደህንነት ስጋቶች አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ በየጊዜው የደህንነት ሪፖርቶችን ይፈትሻል።

## እኔ ለምን መከተብ አለብኝ?

ክትባት መውሰድ በስራ ላይ ደህንነትዎን ለመጠበቅ እንዱሁም እንደገና ከጓደኞችዎ እና ከቤተሰብዎ ጋር ለመገናኘት ይረዳዎታል።

በጠና የመታመም፣ ሆስፒታል የመተኛት ወይም በ COVID-19 የመሞት እድልዎ በጣም አነስተኛ ይሆናል።





ይህ ሰነድ በሌላ ቅርጸት እንዲቀርብልዎት ለመጠየቅ፣ ወደ 1-800-525-0127 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም ኢሜይል ወደ civil.rights@doh.wa.gov ይላኩ፡፡